# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከፌብርዋሪ 21-28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

## እንዲሁም ከማርች 1-10 እና ከማርች 11-20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ


ማርች 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1. እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈው ስምንተ ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምዕራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሸለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግበዋል፡፡ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በጋቲራ 23.3፣ 16.5፣ በአርጆ 22.6፣ በደብረማርቆስ 13፣ በዳንግላ 7.3 እንዲሁም በቡሬ 2.2፣ ሚሜ ይገኙበታል፡፡ ባለፉት ስምንት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን ምዕራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከ2 -39.8 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከተወሰኑት የሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ በስተቀር ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35.0-43.0 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ።




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የፌብርዋሪ የሶስተኛዉ ስምንት ቀናት ከጥቂት የደቡብ ምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ኪስ ቦታዎች በስተቀር አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች በደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር እንደነበር የተሰበሰቡና የተተነተኑ የግብርና ሜቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። በጥቂት ኪስ ቦታዎች ላይ የተገኘው እርጥበት በአካባቢው ለሚበቅሉ ለቋሚ ተክሎች አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 1.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የፌብርዋሪ ስምንት ቀናት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ፀሃያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ የተስተዋለ ሲሆን፤ በአንጻሩ ጥቂት ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ከነዚህም መካከል በጥቂት መካከለኛ አባይ ኪስ ቦታዎች እና በላይኛው ባሮ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው። ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መጠነኛ መሻሻል አውንታዊ ጎን እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር የነበሩ ከመሆኑም በላይ የነበረው ከፍተኛ የውኃ ትነት ጋር ተዳምሮ የውሃ ሀበት መጠንና የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት እንዲቀንስና ከማደረግ አንጻር አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ወር ነው፡፡ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል፡፡ በማርች የሚኖረው የዝናቡ መጠን ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ እስከ 30% የሚያገኙ ሲሆን፤ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ከ20%-40% የሚሆነዉን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ፡፡ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት ለበልግ ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች የዝናቡ መጠንና ስርጭት እየተስፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 7) ፡፡

### 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በሆኑት የመካከለኛዉ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸው የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ቀላል መጠን ያለው ዝናብ የሚያገኙ ቦታዎች

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| | ምስራቅ ቦረና፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ | ቀላል መጠን |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡረጂ፣ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ |
| | ጎፋ፣ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ደቡብ ኦሞ | ቀላል መጠን |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን፣ኤረር፣ሲቲ ዞኖች | ቀላል መጠን |
| አማራ | ዋግ ህምራ፣ ደቡብ ጎንድር፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን |
| | ሰሜን ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ | ቀላል መጠን |
| ትግራይ | የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ዳውሮ፣ ከፋ ሸካ እና ኮንታ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ምስራቅ ጉራጌ፣ሃዲያ፣ ስልጤ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን |
| አዲስ አበባ፤ ድሬደዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን |



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በማርች ወር በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በማርች የመጀመሪያዉ አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ40 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)።



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከማርች 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የወቅቱ ዝናብ አብዛኛውን የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚሸፍን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በመጪዎቹ የማርች ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያወቹ ቀናቶች ላይ በአንጻራዊ ሁኔታ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በደቡብ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ፡፡

## 2.5 እ.ኤ.አ ከማርች 1-10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የማርች የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖር ሲሆንና፤ ይህም ሁኔታ ለበልግ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከበልግ ተለዋዋጭ ባህሪ ጋር ተያይዞ የሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት እና ከፍተኛ የትነት መጠን የአፈር ውስጥ እርጥበት እጥረት እንዲኖር ስለሚያድርግ አርሶ አደሮች፣ አርበቶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት ከታች በተቀመጠው የግብርና ምክረ ሀሳብ መሰረት የቅድም ጥንቃቄ ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት ስምንት ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| የቦረና፣ የምዕራብ ሐረርጌ፣ የጉጂ፣ የምዕራብ ጉጂ፣ የአርሲ፣ የምዕራብ አርሲ፣ የጋሞ፣ የወላይታ፣ የጌድዮ፣ የአማሮ፣ የደራሼ፣ የቡርጂ ዞኖች፣ የዋግህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የደቡብ ጎንደርና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | እርጥበታማ | • የማሳ ዝግጅት ለማድረግ<br>• ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት | • የአፈርና የውኃ እቀባ ማከናወን<br>• የደጋፊ መስኖ የዝናብ ውኃ ማሰባሰብ<br>• በሰብል ማሳ የውኃ መከተር ማከናወን |
| የሰሜን ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች የዳውሮ፣ የከፋ፣ የኮንታ፣ የባሌ፣ የምስራቅ ባሌ፣ የምስራቅ ጅማ፣ የኢሉባቦር፣ የቡኖ በደሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጎፋ፣ የኮንሶ፣ የአሌ፣ የባስኬቶ እና የደቡብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም የዳዋ፣ የሊበን፣ የኤረር፣ የሲቲ፣ የምስራቅ ጉራጌ፣ የሃዲያ እና የስልጤ ዞኖች | መጠነኛ እርጥበት | • ለማሳ ዝግጅት<br>• የመጠጥ ውኃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት | • ዘር ለመዝራት በቂ ያልሆን የአፈር እርጥበት<br>• የመኖ ሰብሎችን ለመዝራት የእርጥበት እጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት | • የአፈርና የውኃ እቀባ ማከናወን<br>• የደጋፊ መስኖ የዝናብ ውኃ ማሰባሰብ<br>• በሰብል ማሳ የውኃ መከተር ማከናወን<br>• ተለዋጭ የእንስሳት መኖ ማከማቸት<br>• የሚገኘውን ውኃ በቁጠባ እና በጥንቃቄ መጠቀም |



ስልክ+2511155383940ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.6 እ.ኤ.አ ከማርች 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ጥቂት የተፋሰስ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በተፋሰሶች ላይ

| የውኃ ተፋሰስና ንዑስ ተፋሰሶች | የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| ገናሌ ዳዋ፣ (የላይኛውና መካከለኛው ንዑስ ተፋሰሶች) | መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል | • በታችኛው ንዑስ ተፋሰስ ደረቅ ሁኔታ<br>• ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን |
| በአባይ ተፋሰስ፣ (በጥቂት የላይኛው ምስራቃዊ ንዑስ ተፋሰሶች) | ዝቅተኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት በመጠኑ መሻሻል | • ከፍተኛ ትነት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት<br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• የግድቦች የውኃ መጠን መቀነስ | • የሚገኘውን የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን |
| ኦሞ ጊቤ፣ (በጥቂት የላይኛው ንዑስ ተፋሰሶች) | | | | |
| አዋሽ፣ (በታችኛው ምስራቃዊ ንዑስ ተፋሰሶች) | | | | |
| በስምጥ ሸለቆ፣(በላይኛው ንዑስ ተፋሰሶች) | | | | |
| ባሮ አኮቦ፣ዋቢ ሸበሌ፣ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ | ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ | | • ከፍተኛ ትነት<br>• የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ | • በተለያዩ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ የሚገኘውን ውኃ |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኦጋዴን፣ አይሻ እና መረብ ጋሽ (በሁሉም ንዑስ ተፋሰሶች) | | | • ንጹህ የመጠጥ ውኃ አርቦት እጥረት<br>• የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ | በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር<br>• የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የቅድመ መስጠንቀቂያና ትንበያዎችን በቅርበት በመከታተል የውኃ አሰተዳደርን መምራት<br>• የውኃ እጥረት በሚገጥማችው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ |



ስልክ+2511155383894ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et